# በወ/ት ብርቱክን ሚደቅሳ ዙሪያ ልዩ ዘገባ - ከአወደ ኢትዮጵያ
# የወ/ት ብርቱካን ሚድቅሳ የሰብአዊ መብት ረገጣ ጉዳይ በፍርድ ቤት

መጋቢት 19 2001 ዓ.ም

አምባገነኑ የሕወሃት አገዛዝ፣ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ሊቀመንበርን፣ ሕገ ወጥ በሆነ መንገድና በማንአለብኝነት፣ በቁጥጥር ሥር ካዋላቸዉ ይኸው ሰባ ዘጠኝ ቀናት አልፈዋል።

ለእዉነትና ለፍትህ በመቆማቸዉ ወ/ት ብርቱካን መታሰራቸዉ ሳያንስ፣ ሕወሃት እኚህን ሴት በማንም ሌላ ነፍሰ ገዳይ እስረኛ እንኳን ያልተደረገ ግፍ እየፈጸመባቸዉ ነዉ። ሁለት ሜትር በሁሉት በሁለት ሜትር ባለች ክፍል ዉስጥ በጨለማ እንዲቀመጡ የተደረጉ ሲሆን፣ ሕገ መንግስታዊ መብታቸዉ ተጥሶ፣ በዘምድ በሐኪም በመንፈሳዊ አባትና በጠበቃዎቻዉ እንዳይጎበኙ ታግደዋል።

ይህ በወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ላይ እየደረሰ ያለዉ ኢሰብአዊ ግፍና ጭካኔ ብዙዎችን ከማስቆጣቱ ባሻገር፣ ገዢዉ ፓርቲ እንደሚለዉ "ሕግን የማስከበር ሂደት" እየፈጸመ ሳይሆን ከፍተኛ የሆነ የጭከናና የ"ቶርቸር" ዘመቻ በእኚህ ቆራጥ ሴት ላይ እያደረገ እንደሆኖ በግልጽ የሚያሳይ ነዉ።

ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን እንዳይጎበኙ ከተከለከሉት አንዱ የወ/ት ጠብቃ አቶ ተስፋዬ ቱሉ ናቸዉ። አቶ ተስፋዬ ቱሉ የፍትህ ሚኒሰቴር ከሕግ መንግስቱ ዉጭ፣ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ዘምድ እንዳይጠይቃቸዉ፣ ጠበቃቸዉ፣ ሐኪሞችንና መንፈሳዊ አባቶችን እንዳይጎበኟቸዉ ማስደርጉን ሕገ ወጥ ተግባር እንደሆነ በመግለጽ፣ በፍትህ ሚኒስቴር ላይ ክስ የካቲት 27 2001 ቀን አቅርበዉ ነበር። በቀረበዉም ክስ መሰረት፣ የልደታ ምድብ ዘጠነኛ የፍትሃብሄር ችሎት ክሱ መቀጠል እንዳለበትና እንደሌለበት ለመወሰን ዛሬ መጋቢት ዘጠኝ ቀን ጉዳዮን ለማዳመጥ ተቀምጦ ዉሏል።

ፍርድ ቤቱ በፍትህ ሚኒስቴር ላይ የደረሰዉን ክስ ተገቢና መደመጥ ያለበት እንደሆነ በመወሰን፣ ተለዋጭ ቀጠሮ ለመጋቢት 24 ቀን 2001 እንደሰጠ ከስፍራዉ የደረሰን ዜና ያመለክታል። በዚያ ቀን የፍትህ ሚኒስቴር ቀርቦ መልስ እንዲሰጥም ፍርድ ቤቱ እንዳዘዘ ለማወቅ ችለናል።

በዛሬዉ የፍርድ ቤት ዉሎ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ በአካል በፍርድ ቤቱ ያልተገኙ ሲሆን ጉዳዩን በግንባርና በቀርበት ለመከታተል የአንድነት ከፍተኛ የአመራራ አባላት በፍርድ ቤቱ ተገኝተዉ እንደነበረም ለማወቅ ችለናል።

ያነጋገርናቸዉ የፖለቲካ ተንታኞች፣ ሕወሃት ፍርድ ቤቶችን የሚቆጣጠር እንደመሆኑ የዛሬዉ የፍርድ ቤት ዉሳኔ በኢትዮጵያ የሕግ ስርዓት እንዳለ ለማሳየትና ጉዳዩን ለመጎተት የታቀደ እንደሆነ ገልጸዉ፣ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ በእሥር ቤት ሳሉ የሰብአዊ ና ሕገ መንግስታዊ መብታቸዉ እንዲጠበቅ ለማድረግ እየተሞከረ ያለ ሂደት እንጂ ወይዘሪቷ ከእሥር ቤት እንዲፈቱ ለማድረግ የሚያስችል ሂደት እንዳልሆነም አስረድተዋል።

በዚህም ምክንያት ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን ለማስፈታት የሚደረገዉ ትግል መጠናከር እንዳለበትና ገዢዉ ፓርቲ ተገዶ እንዲፈታ ካልተደረገ በቀር በሚቆጣጠራቸዉ ፍርድ ቤቶች መፍትሄ ይገኛል ማለት አስቸጋሪ እንደሆነ ተንታኞቹ አክለዋል።

በተያያዘ ዜና የአንድነት ፓርቲ አመራር አባላት ነገ መጋቢት 10 ቀን ከአሜሪካዉ አምባሳደር ዶናልድ ያማማቶ ጋር በወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ በግፍ መታሰር ዙሪያ ዉይይት እንደሚያደርጉ ለማወቅ ችለናል። ያለፈዉ ሳምንት የአሜሪካን ኤምባሲ ባለሥልጣናት የወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን እናት፣ ወይዘሮ አልማዝ ገብረእግዚአብሄርን አስጠርተዉ ወ/ት ብርቱካን ያሉበትን ሁኔታ በሰፊዉና በጥልቀት መጠየቃቸዉ ይታወሳል።